# ትምህርት 38

1. እስራኤላውያን ውኃ ባጡ ጊዜ እግዚአብሔር ውኃ እንደሚሰጣቸው አምነው ነበር?

ሀ- አላመኑም።

2. እስራኤላውያን ውኃ ባጡበት ወቅት ምን ማድረግ ነበረባቸው?

ሀ- እግዚአብሔር ውኃ እንዲሰጣቸው መለመን ነበረባቸው።

3. ውኃ ለማውጣት ሙሴ ምን እንዲያደርግ እግዚአብሔር አዘዘው?

ሀ- ሙሴን ለዐለቱ እንዲናገር እግዚአብሔር አዘዘው።

4. ሙሴና አሮን ለዓለቱ በመናገር ፈንታ ስለመቱት እግዚአብሔር ቀጥቶአቸው ነበር?

ሀ- አዎን።

5. እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን የቀጣቸው በምን ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር ወደ ከነዓን ምድር እንዳይገቡ በማድረግ ቀጣቸው።

6. እስራኤላውያን ማጉረምረማቸውን ስለ ቀጠሉ እግዚአብሔር ምን አደረገባቸው?

ሀ- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ብዙ መርዛማ እባቦችን በመላክ ቀጣቸው።

7. ኃጢአት ከእባብ ጋር በምን ይመሳሰላል?

ሀ- እባቦች እስራኤላውያንን ነድፈው እንደ ገደሏቸው ሁሉ ኃጢአትም ሰዎችን ነድፎ ይገድላል።

8. እግዚአብሔር ሙሴ እስራኤላውያንን ለማዳን ምን እንዲያደርግ ነገረው?

ሀ- ከነሐስ እባብ እንዲሠራና በእንጨት ላይ እንዲሰቅለው ነገረው።

9. እስራኤላውያን ከሞት ለመዳን ምን ማድረግ ነበረባቸው?

ሀ- በእንጨት ላይ የተሰቀለውን የናስ እባብ መመልከት ነበረባቸው።

10. በእንጨት ላይ የተሰቀለውን የናስ እባብ የተመለከቱት እስራኤላውያን በሕይወት ኖሩ?

ሀ- አዎን።

11. የናሱ እባብ እስራኤላውያንን የማዳን ኃይል ነበረው?

ሀ- አልነበረውም።

12. እስራኤላውያንን የማዳን ኃይል ያለው ማን ብቻ ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር።

13. የእስራኤላውያን ኃጢአት ሞትን አምጥቶባቸዋል?

ሀ- አዎን።

14. የእስራኤላውያን ኃጢአት ሞት ቢያመጣባቸውም ወደ ናሱ እባብ ለተመለከቱት እግዚአብሔር ምን አደረገላቸው?

ሀ- እግዚአብሔር አዳናቸው።

- እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ስላላመኑ ወደ ከነዓን አልገቡም።

- እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ስላላመኑ ሁሉም ጐልማሶች እስኪያልቁ ድረስ በምድረ በዳ ለአርባ ዓመታት ተንከራተቱ።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን የቀጣው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም ሙሴ ወደ እነርሱ ባመጣው በእግዚአብሔር ቃል ለማመን ስላልፈለጉ ነው።

- ሙሴ የእግዚአብሔርን ቃል ወደ እስራኤላውያን እንዳመጣ ሁሉ እኔም የእግዚአብሔርን ቃል ወደ እናንተ አምጥቻለሁ።

- እናንተም እንደ እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ቃል ለማመን ካልፈለጋችሁ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን እንደ ቀጣ ሁሉ እናንተንም ይቀጣችኋል።

- ከአርባ ዓመታት በኋላ እንዲሁም ሁሉም ጐልማሳ እስራኤላውያን ከሞቱ በኋላ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን እንደገና ወደ ከነዓን ድንበር መራቸው።

- ሙሴ የእግዚአብሔርን ትዛዝ ስለተላለፈ፥ እስራኤላውያንን እየመራ ወደ ከነዓን ይገባ ዘንድ እግዚአብሔር አልፈቀደለትም።

- እግዚአብሔር ሙሴ እስራኤላውያንን ይዞ ወደ ከነዓን ምድር እንዲገባ ስላልፈቀደ ሌላ መሪ መረጠላቸው።

ዘኁልቁ 27፡18-20 & 22-23

18- ስለዚህ እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፤ «መንፈስ ቅዱስ ያደረበትን የነዌን ልጅ ኢያሱን ወስደህ እጅህን ጫንበት።

19- በካህኑ በአልዓዛርና በመላው ማኅበር ፊት እንዲቆም አድርገው፤ በፊታቸውም ሹመው፤

20- መላው የእስራኤል ማኅበረ ሰብ እንዲታዘዝለትም ከሥልጣንህ ከፍለህ ስጠው።

22- ሙሴም እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ፤ ኢያሱንም ወስዶ በካህኑ በአልዓዛርና በመላው የእስራኤል ማኅበር ፊት አቆመው፤

23- ከዚያም እግዚአብሔር በሙሴ አማካይነት ባዘዘው መሠረት እጁን በራሱ ላይ ጭኖ ሾመው።

- እግዚአብሔር በሙሴ ምትክ የመረጠው አዲሱ መሪ ማን ነበር?

- ኢያሱ።

- ኢያሱ የእስራኤላውያን መሪ ከሆነ በኋላ እግዚአብሔር ሙሴን በከነዓን አጠገብ ወደሚገኘው አንድ ተራራ ላይ እንዲወጣ ነገረው።

- በተራራው ጫፍ ላይ እግዚአብሔር ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብና ለዘሮቻቸው ቃል የገባውን የከነዓንን ምድር አሳየው።

ዘዳግም 34፡1-4

1- ሙሴ ከሞአብ ሜዳ ተነሥቶ ለኢያሪኮ ትይዩ ወደሆነው ፈስጋ ጫፍ፣ ወደ ናባው ተራራ ወጣ። በዚያም እግዚአብሔር ምድሪቱን ሁሉ አሳየው፤ ይኸውም ከገለዓድ እስከ ዳን፥

2- ንፍታሌምን ሁሉ፣ የኤፍሬምንና የምናሴን ግዛት፣እስከ ምዕራብ ባሕር ድረስ ያለውን የይሁዳን ምድር ሁሉ፥

3- ኔጌብንና የዘንባባ ከተማ ከሆነችው ከኢያሪኮ ሸለቆ እስከ ዞዓር ያለውን ምድር ሁሉ ነው።

4- ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር ሙሴን «ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ፣ 'ለዘሮቻችሁ እሰጣለሁ' ብዬ በመሐላ ቃል የገባሁላቸው ምድር ይህች ናት። በዐይንህ እንድታያት አድርጌአለሁ፤ ነገር ግን ወደዚያ አትሻገርም» አለው።

- ሙሴ እግዚአብሔርን ስላልታዘዘ ወደ ከነዓን እንዲገባ እግዚአብሔር አልፈቀደለትም።

- እግዚአብሔር ለሙሴ የተናገረውን ቃል በመፈጸም ወደ ከነዓን ምድር እንዳይገባ አደረገው?

- አዎን።

- እግዚአብሔር ሁልጊዜ ቃሉን ይፈጽማል።

- እግዚአብሔር የተናገረውን ቃል ፈጽሞ አይሽርም።

- እግዚአብሔር ለሙሴ የከነዓንን ምድር ከተራራው ጫፍ ካሳየው በኋላ ሙሴ ሞተ።

ዘዳግም 34፥5

5- እግዚአብሔር እንደተናገረው የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ በሞዓብ ምድር ሞተ።

- ሙሴ ከሞተ በኋላ እግዚአብሔር ኢያሱን ተናገረው።

- እግዚአብሔር ኢያሱን ወደ ከነዓን ለመግባት እንዲዘጋጅ ነገረው።

ኢያሱ 1፥1-2

1- የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ ከሞተ በኋላ፣ እግዚአብሔር የሙሴን አገልጋይ የነዌን ልጅ ኢያሱን እንዲህ አለው፤

2- «እነሆ፣ ባሪያዬ ሙሴ ሞቶአል፤ አሁንም አንተና ይህ ሕዝብ ሁሉ ተነሡ፤ ለእስራኤላውያን ወደምሰጣቸው ምድር ለመግባት የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻገሩ።

- ሙሴ ከሞተ በኋላ ኢያሱ እስራኤላውያንን ወደ ከነዓን ምድር መራቸው።

- እግዚአብሔር ቃሉን በመጠበቅ ለአብርሃም ዘሮች የከነዓንን ምድር አወርሷቸዋል?

- አዎን።

- እግዚአብሔር ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ በገባው ቃል መሠረት የከነዓንን ምድር ለእስራኤላውያን ሰጣቸው።

- ሰይጣንና ፈርዖን እስራኤላውያንን በግብፅ በባርነት ለማቆየት ሞከሩ።

- ነገር ግን እግዚአብሔር ከነዓንን ለእስራኤላውያን ለመስጠት የገባውን ቃል ፈጸመ።

- እስራኤላውያን እግዚአብሔር ምግብና መጠጥ በበረሃ እንደሚሰጣቸው አላመኑም ነበር።

- ነገር ግን እግዚአብሔር ከነዓንን ለእስራኤላውያን ለመስጠት የገባውን ቃል ፈጸመ።

- እግዚአብሔር ሁልጊዜም የገባውን ቃል ይፈጽማል።
- እግዚአብሔር ከገባቸው ተስፋዎች አንዱን እንኳ አያፈርስም።

ኢያሱ 11፡23ሀ

23- ስለዚህ ኢያሱ እግዚአብሔር ሙሴን ባዘዘው መሠረት ምድሪቱን በሙሉ ያዘ፤ እንደ ነገዳቸው አከፋፈል በመመደብም ርስት አድርጎ ለእስራኤላውያን ሰጣቸው።

- አሁን እስራኤላውያን በከነዓን መኖር ጀምረዋል።

- ኢያሱ በሕይወት እስከቆየበት ጊዜ ድረስ እስራኤላውያን እግዚአብሔርን አመለኩ።

መሳፍንት 2፡7

7- ኢያሱ በሕይወት በነበረበት ዘመን ሁሉ፥ እንዲሁም ከእርሱ በኋላ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ያደረገውን ታላላቅ ነገሮች ሁሉ ያዩ አለቆች በነበሩበት ዘመን ሁሉ፥ ሕዝቡ እግዚአብሔርን አመለከ።

- ከጥቂት ጊዜ በኋላ ኢያሱ አርጅቶ ሞተ።

መሳፍንት 2፡8-9

8- የእግዚአብሔር አገልጋይ የነዌ ልጅ ኢያሱ በመቶ አሥር ዓመቱ ሞተ።

9- እነርሱም በኰረብታማው በኤፍሬም አገር በምትገኘው ከገዓስ ተራራ በስተ ሰሜን ባለችው በራሱ ርስት ላይ በተምናሔሬስ ቀበሩት።

- ኢያሱ በሕይወት በነበረበት ዘመን ሁሉ እስራኤላውያን እግዚአብሔርን አመለኩ።

- ኢያሱ ከሞተ በኋላ እስራኤላውያን ምን አደረጉ?

መሳፍንት 2፡ 10-13

10- ያ ሁሉ ትውልድ ወደ አባቶቹ ከተከማቸ በኋላ እግዚአብሔርንም ሆነ እርሱ ለእስራኤል ሕዝብ ያደረገውን ነገር የማያውቅ ሌላ ትውልድ ተነሣ።

11- ከዚያም እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገር አደረጉ፤

12- የበዓል አማልክትንም አመለኩ። ከግብፅ ምድር ያወጣቸውን የአባቶቻቸውን አምላክ እግዚአብሔርን ተዉ፤ በዙሪያቸው ያሉት ሕዝቦች የሚያመልኳቸውን አማልክት ተከተሉ፤ ሰገዱላቸውም።

13- እግዚአብሔርንም አስቈጡት፣ እርሱን ትተው በዓልንና አስታሮትን አምልከዋልና።

- ኢያሱ ከሞተ በኋላ እስራኤላውያን እግዚአብሔርን በመተዉ በጣም ክፉዎች ሆኑ።

- ኢያሱ ከሞተ በኋላ እስራኤላውያን ጣዖት ሠርተው በእግዚአብሔር ምትክ አመለኳቸው።

- የእስራኤላውያን ጐረቤት ሆነው የሚኖሩት ከነዓናውያን በዓልና አስታሮት የሚባሉ ጣዖቶችን ያመልኩ ነበር።

- እስራኤላውያን እግዚአብሔርን በመተዉ በዓልንና አስታሮትን አመለኩ።

- እስራኤላውያን እግዚአብሔርን እንዲተዉና ጣዖቶችን እንዲያመልኩ ያሳታቸውን ማን ነበር?

- ሰይጣን።

- ሰይጣን ሕዛቡን ስላሳተ ሕዝቡ እግዚአብሔርን እያመለከ እንደ ሆነ ያስብ ነበር።

- ነገር ግን ሕዝቡ እግዚአብሔርን እያመለከ አልነበረም።

- ሕዝቡ በበዓልና በአስታሮት ጣዖቶች ውስጥ ራሱን የደበቀውን ሰይጣንን ያመልኩ ነበር።

- ሰይጣን አዳምና ሔዋንን ለማሳት በእባቡ ውስጥ እንደ ተደበቀ ሁሉ ሕዝቡን ለማሳት በበዓልና በአስታሮት ጣዖቶች ውስጥ ተደበቀ።

- ሰይጣን በመናፍስትና በዘር አምልኮ በስተጀርባ ይደበቃል።

- ሰዎች መናፍስትንና ከዘር የመጣውን አምልኮ ሲያመልኩ እግዚአብሔርን ያመለኩ ያህል ሊያስቡ ይችላሉ።

- ነገር ግን ሰይጣንን እንጂ እግዚአብሔርን እያመለኩ አይደለም።

- እኛ ከእግዚአብሔር ውጭ የምናመልከው ነገር ካለን ማንን እያመለክን ነው?

- ሰይጣንን።

- ሰይጣን ሰዎች የተቀረጹ ምስሎችን እንዲያመልኩ የሚመራቸው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም ሰይጣን እግዚአብሔርን ስለሚጠላ ማንም እርሱን እንዲያመልክ ስለማይፈልግ ነው።

- ሰይጣን ሁሉንም ሰዎች ስለሚጠላ ማንንም እግዚአብሔር እንዲያድን አይፈልግም።

- እስራኤላውያን በዓልንና አስታሮትን ያመልኩ እንደ ነበር እግዚአብሔር ያውቅ ነበር?
- አዎን።

- እስራኤላውያን በዓልንና አስታሮትን በማምለካቸው እግዚአብሔር ተቆጥቶ ነበር?

- አዎን።

- እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ላይ ምን አደረገባቸው?

መሳፍንት 2፥14-15

14- እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ በመቈጣቱ ለሚዘርፏቸው አሳልፎ ሰጣቸው፣ በዙሪያቸው ላሉ ጠላቶቻቸው ሸጣቸው።

15- እስራኤላውያን ለውጊያ በሚወጡበት ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔር አስቀድሞ በእርሱ ላይ እንደ ተናገረውና እንደማለው ይሸነፉ ዘንድ የእግዚአብሔር እጅ ትከፋባቸው ነበር፤ ከዚህም የተነሣ እጅግ ተጨነቁ።

- እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ከማምለክ ይልቅ በዓልንና አስታሮትን ስላመለኩ እግዚአብሔር ቀጥቶአቸው ነበር።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያን ምስሎችን በማምለካቸው በምን ቀጣቸው?

- እግዚአብሔር የእስራኤላውያን ጠላቶች መጥተው ሰብሎቻቸውን ሁሉ እንዲያጠፉባቸው አደረገ።

- እግዚአብሔር የእስራኤላውያን ጠላቶች መጥተው ከብቶቻቸውን ሁሉ እንዲሰርቁ አደረገ።

- እግዚአብሔር የእስራኤላውያን ጠላቶች መጥተው እስራኤላውያንን ባሪያዎች እንዲያደርጓቸው አደረገ።

- እስራኤላውያን ኃጢአታቸውን በተናዘዙና እግዚአብሔር እንዲያድናቸው በሚለምኑበት ጊዜ፥ እግዚአብሔር ምን ያደረግ ነበር?

መሳፍንት 2፡16

16- እግዚአብሔርም ከእነዚህ ወራሪዎች የሚያድኗቸውን መሳፍንት አስነሣ።

- እስራኤላውያን ኃጢአታቸውን በተናዘዙና እግዚአብሔር እንዲያድናቸው በሚለምኑበት ጊዜ፥ እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን መካከል የሚመሯቸውን ወንዶችና ሴቶችን እየመረጠ ጠላቶቻቸውን እንዲያሸንፉ ያደርግ ነበር።

- እስራኤላውያን ጠላቶቻቸውን እንዲያሸንፉ ለማድረግ እግዚአብሔር የመረጣቸው ወንዶችና ሴቶች ምን ይባሉ ነበር?

- መሳፍንት።

- እግዚአብሔር የመረጣቸው መሳፍንት በነበሩባቸው ዘመናት ሁሉ እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ይከተሉ ነበር።

- እግዚአብሔር የመረጣቸው መሳፍንት ሲሞቱ እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ፊንታ ጣዖቶችን ወደ ማምለክ ይመለሱ ነበር።

መሳፍንት 2፥ 17-19

17- እስራኤላውያን ግን ሌሎችን አማልክት ተከትለው አመነዘሩ፤ ሰገዱላቸውም እንጂ መሳፍንታቸውን አልሰሙም። አባቶቻቸው እግዚአብሔርን በመታዘዝ በሄዱበት መንገድ ሳይሆን፣ አባቶቻቸው የእግዚአብሔርን ሕግ በመከተል ከሄዱበት መንገድ ፈጥነው ፈቀቅ አሉ።

18- እግዚአብሔር መሳፍንትን በስነሣላቸው ቍጥር ከመስፍኑ ጋር ስለሚሆን፣ እርሱ በሕይወት እስካለ ድረስ እግዚአብሔር ከጠላቶቻቸው ያድናቸው ነበር፤ ከጠላቶቻቸው ሥቃይና መከራ ሲደርስባቸው በሚጮኹበት ጊዜ እግዚአብሔር ይራራላቸው ነበር።

19- መስፍኑ ከሞተ በኋላ ግን ሕዝቡ ሌሎችን አማልክት በመከተል፣ እነርሱን በማገልገልና በማምለክ ከአባቶቻቸው ይልቅ ወደ ክፉ መንገድ ተመለሱ፤ ክፉ ሥራቸውንና የእልኸኝነት መንገዳቸውንም አይተዉም ነበር።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያን በኃጢአታቸው ምክንያት ቢቀጣቸውም እንኳ ይወዳቸውና ይጠብቃቸው ነበር።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን መውደድና መጠበቁን የቀጠለው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ ታላቅ ሕዝብ የሚሆኑ ብዙ ዘሮችን እንደሚሰጣቸው ቃል ገብቶ ስለነበር ነው።

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ዘር አዳኝ እንደሚልክ ቃል ገብቶ ስለነበር ነው።

- ምክንያቱም እግዚአብሔር መልእክቱን መጽሐፍ ቅዱስን በእስራኤላውያን ዘር በኩል ሊልክ ቃል ገብቶ ስለነበር ነው።

- እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ቃሉን ሰምተው እንዲድኑ ይፈልጋል።

- የመጨረሻው የእስራኤላውያን መስፍን ማን ይባል ነበር።

- ሳሙኤል

- ሳሙኤል ለበርካታ ዓመታት የእስራኤል መስፍን ነበር።

- ሳሙኤል ባረጀበት ወቅት እርሱን የሚተካ ማንም ሰው አልነበረም። ምክንያቱም የሳሙኤል ልጆች እግዚአብሔርን የማያምኑ ስለነበር ነው።

1ኛ ሳሙኤል 8፡1-3

1- ሳሙኤል በሸመገለ ጊዜ፣ ልጆቹን ፈራጆች አድርጎ በእስራኤል ላይ ሾማቸው።

2- የበኵር ልጁ ኢዮኤል ሲሆን፣ ሁለተኛው ልጁ አብያ ነበረ፤ እነርሱም በቤርሳቤህ ይፈርዱ ነበር።

3- ነገር ግን ልጆቹ የአባታቸውን ፈለግ አልተከተሉም፤ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ሲሉ ከመንገዱ ወጡ፤ ጉቦ ተቀበሉ፤ ፍርድ አጣመሙ።

- ሳሙኤል ስላረጀና እርሱን የሚተካ ሰው ስላልነበረ እስራኤላውያን በአንድነት ተሰብስበው ወደ ሳሙኤል መጡ።

1ኛ ሳሙኤል 8፡4-6

4- ስለዚህ የእስራኤል ሽማግሌዎች ሁሉ በአንድነት ተሰብስበው ሳሙኤል ወዳለበት ወደ አርማቴም መጡ።

5- እነርሱም «አንተ አርጅተሃል፤ ልጆችህ ያንተን ፈለግ አይከተሉም፤ ስለዚህ ሌሎች ሕዝቦች እንደሚያደርጉት ሁሉ የሚመራን ንጉሥ አንግሥልን» አሉት።

6- ነገር ግን «የሚመራን ንጉሥ አንግሥልን» ማለታቸው ሳሙኤልን አላስደሰተውም፤ ስለዚህ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ።

- ሳሙኤል ከመሞቱ በፊት፣ እስራኤላውያን ምን እንዲያደርግላቸው ጠየቁት?

- እስራኤላውያን፣ ሳሙኤልን የሚመራቸውን ንጉሥ እንዲያነግሥላቸው ጠየቁት።

- በዚህ ጥያቄ ሳሙኤል ያዘነው ለምን ነበር?

- ሳሙኤል ያዘነው፣ እስራኤላውያን እግዚአብሔር ንጉሣቸው እንዲሆን ባለመፈለጋቸው ነበር።

- እስራኤላውያን ከግብፅ በወጡበት ጊዜ ንጉሣቸው ማን ነበር?
- እግዚአብሔር።

- በምድረ በዳ በተጓዙበት ወቅት የእስራኤላውያን ንጉሥ ማን ነበር?
- እግዚአብሔር።

- በምድረ በዳ ምግብና ውኃ በተሰጣቸው ጊዜ፣ ንጉሣቸው ማን ነበር?
- እግዚአብሔር።

- የከነዓን ምድር በተሰጣቸው ጊዜ የእስራኤላውያን ንጉሥ ማን ነበር?
- እግዚአብሔር።

- ለብዙ ዓመታት እግዚአብሔር የእስራኤላውያን ንጉሥ ነበር።

- ከግብፅ ባርነት ነፃ ካወጣቸው ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔር ንጉሣቸው ነበር።

- አሁን ግን እስራኤላውያን እግዚአብሔር ንጉሣቸው እንዲሆን አልፈለጉም።

- እስራኤላውያን በአጠገባቸው እንደሚኖሩት፣ የሰው ንጉሥ እንዳላቸው ክፉ ሕዝቦች ለመሆን ፈለጉ።

- እስራኤላውያን፣ እግዚአብሔር ንጉሣቸው እንዳይሆን ፈለጉ።

- እግዚአብሔር ለሳሙኤል ይህን ነገረው።

1ኛ ሳሙኤል 8፡7-8

7- እግዚአብሔርም ሳሙኤልን እንዲህ አለው፤ «ንጉሣቸው እንዳልሆን የናቁት እኔን እንጂ አንተን አይደለምና ሕዝቡ የሚሉህን ሁሉ አድምጥ።

8- ከግብጽ ምድር ካወጣኋቸው ዕለት አንሥቶ እስከ ዛሬ ድረስ እኔን ትተው ሌሎች አማልክትን በማምለክ ያደረጉትን ሁሉ በአንተም ላይ እያደረጉ ነው። »

- እግዚአብሔር ሳሙኤልን ምን አለው?

- እግዚአብሔር ሳሙኤልን እስራኤላውያን የናቁት እርሱን እንዳልሆነ ነገረው።

- እግዚአብሔር ሳሙኤልን እስራኤላውያን ንጉሥ መፈለጋቸው እግዚአብሔር ንጉሣቸው እንዳይሆን መፈለጋቸው መሆኑን ነገረው።

- እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ንጉሥ ሰጣቸው?

1ኛ ሳሙኤል 11፡14-15

14- ከዚያም ሳሙኤል ሕዝቡን «ኑና ወደ ጌልገላ እንሂድ፤ ንግሥናውንም እናጽና» አለ።

15- ሕዝቡ ሁሉ ወደ ጌልገላ ሄደ፤ የሳኦልንም ንጉሥነት በእግዚአብሔር ፊት አጸና። በዚያም ሕዝቡ የኅብረት መሥዋዕት በእግዚአብሔር ፊት አቀረበ፤ ሳኦልና እስራኤላውያንም ሁሉ ታላቅ በዓል አደረጉ።

- እስራኤላውያን እግዚአብሔር ንጉሣቸው እንዲሆን ባይፈልጉም እንኳን እግዚአብሔር ሌላ ንጉሥ ሰጣቸው።

- ስሙም ሳኦል ነበር።

- የእስራኤላውያን ንጉሥ ተብሎ የተጠራ የመጀመሪያው ሰው ሳኦል ነበር።